የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፬
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፪

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

6[th] Year No. 44
ADDIS ABABA - 6[th] July, 2000

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፪፻፲፬/፲፱፻፺፪ ዓ.ም.
ከሩሲያ ፌዴሬሽን መንግሥት ጋር ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት የተደረገው ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ................................ ገጽ ፩ሺ፫፻፹፪

CONTENTS

Proclamation No. 214/2000
The Investments Promotion and Reciprocal protection Agreement with the Government of the Russian Federation Ratification Proclamation ..... Page 1382

## አዋጅ ቁጥር ፪፻፲፬/፲፱፻፺፪

## ከሩሲያ ፌዴሬሽን መንግሥት ጋር ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት የተደረገው ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በሩሲያ ፌዴሬሽን መንግሥት መካከል ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት እና ዋስትና ለመስጠት የካቲት ፪ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም. ሞስኮ ላይ ስምምነት የተፈረመ ስለሆነ፤

ስምምነቱ በሚገባ ሥራ ላይ የሚውለው በተዋዋይ ሀገር ሕጎች መሠረት ስምምነቱ መፅደቁን የሚያረጋግጡ ሰነዶች በዲፕሎማቲክ አካላት አማካኝነት ልውውጥ ከተደረገ በኋላ እንደ ሚሆን በስምምነቱ ውስጥ የተገለፀ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት ከዚህ እንደሚከተለው ታውጇል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ከሩሲያ ፌዴሬሽን መንግሥት ጋር ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት የተደረገው ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፪፻፲፬/፲፱፻፺፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 214/2000

## *A PROCLAMATION TO RATIFY THE INVESTMENTS PROMOTION AND RECIPROCAL PROTECTION AGREEMENT WITH THE GOVERNMENT OF THE RUSSIAN FEDERATION*

WHEREAS, an Agreement, on the promotion and Reciprocal profection of Investements, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Russian Federation; was signed in Moscow, on the 10[th] day of February, 2000;

WHEREAS, it is stipulated in the Agreement that the Agreement shall enter into force on the date of exchange of instruments of ratification through diplomatic channel;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Agreement at its session held on the 6[th] day of July, 2000;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

   This Proclamation may be cited as the "Investments Promotion and Reciprocal Protection Agreement with the Government of the Russian Federation Ratification Proclamation No. 214/200."

፪· <u>ስምምነቱ ስለመጽደቁ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በሩሲያ ፌዴሬሽን መንግሥታት መካከል ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና ዋስትና ለመስጠት የካቲት ፪ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም. በሞስኮ ከተማ የተፈረመው ስምምነት ጸድቋል።

፫· <u>የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን ሥልጣን</u>

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬· <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሰኔ ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2. *Ratification of the Agreement*

The Agreement, on Promotion and Reciprocal Protection of Investments, signed in Moscow on the 10th day of February, 2000, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Russian Federation, is ratified.

3. *Power of the Ethiopian Investment Authority*

The Ethiopian Investment Authority is hereby empowered to implement the Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 6th day of July, 2000.

Done at Addis Ababa, this 6th day of July, 2000.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE